# አዲስ ምዕራፍ

## ዓመታዊ መጽሄት




**በህዝብ ግንኙነትና**
**ኮሙኒኬሽን የተዘጋጀ**
**ሐምሌ 2015 ዓ/ም**
**አዲስ አበባ**

address




**የአዲስ ምዕራፍ ትርጓሜ**

በለውጡ ማግስት ታሪካዊው በሆነው በ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ
የከተማው ነዋሪ ጸሀይና ዝናብ ሳይበግረው በነቂስ ወጥቶ
መምረጡ የሚታወስ ነው፡፡ ይህን የህዝብ ጥያቄና በምርጫ ወቅት ቃል
በገቡት መሰረት አደራቸውን ለመወጣት
የሚያስችላቸውን ተግባር ማከናወንን ታሳቢ ያደረገ ልዩ ስያሜ ነው፡፡

## የምክር ቤቱ ርዕይ

በ2018 ዓ.ም በከተማው ፖሊሲዎችና ሕጎች ተተግብረው የህዝብ ተጠቃሚነት ተረጋግጦ ማየት፤

## የምክር ቤቱ ተልዕኮ

የምክር ቤት አቅም በመገንባት የከተማውን ህዝብ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ አሳታፊ ፖሊሲና ህጎችን በማውጣት፣ የተጠያቂነት ስርዓትን በመዘርጋት የህዝቡን እርካታ የሚያረጋግጥ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግና አሰራሮችን በማዘመን ዴሞክራሲያዊና ሚዛናዊ የመንግስት መዋቅራዊ ሚናን የሚያስጠብቅ ምክር ቤት መገንባት ነው፡፡

## የምክር ቤቱ እሴቶች

- የህግ የበላይነት
- ብዝሃነት
- አሳታፊነት
- ታማኝነት
- ቅንነት
- ቁርጠኝነት
- ተደራሽነት
- ምላሽ ሰጪነት
- ተጠያቂነት

# የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር

የምክር ቤቱ ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነቶች በሚከተሉት የሕግ ማዕቀፎች የተደነገጉት ናቸው፤ እነዚህም፣

- በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 49 ንኡስ አንቀፅ 2 እና 4
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 11 ንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 እንዲሁም አንቀጽ 14 ንኡስ አንቀፅ 1 እና 2፤
- በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የአባላት የአሠራርና የሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 1፣ 2 እና 3 የቀረቡ ናቸው።

በተጨማሪም፣ ከምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር የተወሰኑት በውክልና የተሰጠው የምክር ቤት ጽ/ቤት በተሻሻለው የማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 80/2015 የተደነገገ ተግባራትን ያከናውናል።

**ማውጫ**


1. የምክር ቤቱ ራዕይ------------------------------------------------------------------------------------
2. የምክር ቤቱ ተልዕኮ-----------------------------------------------------------------------------------
3. የምክር ቤቱ እሴቶች----------------------------------------------------------------------------------
4. ምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር---------------------------------------------------------------------------

1. መልዕክት---------------------------------------------------------------------------------------------2
2. የምክር ቤቱ የ2015 ዓ/ም የጉባኤ እንቅስቃሴ ----------------------------------------------------------6
3. የምክር ቤቱ የክትትልና ቁጥጥር ስራ-----------------------------------------------------------------------7
   - የመንግስት በጀት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ----------------------------15
   - የንግድ ኢንዱስትሪ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ-------------------------------------------16
   - የከተማ ልማትና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ---------------------------------------------17
   - የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ-------------------------------------------------19
   - የመሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ-----------------------------------------20
   - ሴቶችና ማህበራዊ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ--------------------------------------------------22
   - የሰላም፣የፍትህና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ------------------------------------23

4. የምክር ቤት ጽ/ቤት-----------------------------------------------------------------------------------25
5. የትስስር አደረጃጀት-----------------------------------------------------------------------------------27
6. ሴት የም/ቤት አባላት ኮከስ-------------------------------------------------------------------------33
7. ብሔራዊ ባዓላት አከባበር---------------------------------------------------------------------------34
   - ሰንደቅ ዓላማ-----------------------------------------------------------------------------------34
   - የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን----------------------------------------------------36
8. አረንጓዴ አሻራ ልማት ለሀገር እና አካባቢ ልማት-------------------------------------------------------41
9. የክፍለ ከተማ ምክር ቤቶች እንቅስቃሴ-------------------------------------------------------------45
10. የ2015 በጀት ዓመት የተካሄዱ ጉባኤዎችና አጀንዳዎች----------------------------------------------48
11. የፀደቁ አዋጆች ዝርዝር ----------------------------------------------------------------------------49
12. ፎቶ ማህደር---------------------------------------------------------------------------------------50


3ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት




**የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ቡዜና አልከድር**

# መልዕክት

የተወደዳችሁ የዚህ መፅሄት አንባቢያን የሆናችሁ የአዲስ አበባ ከተማ ም/ቤት አባላት እና የከተማዋ ነዋሪዎች ፣እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ፤

የአዲሱ ምዕራፍ ምክርቤታችን ለከተማው ብሎም ለሀገር እድገት ጉልህ ሚና ያላቸውንና የነዋሪውን ጥቅም የሚያስጠብቁ ህጎችን በማውጣት የከተማ አስተዳደሩን አስፈፃሚ አካላት አፈፃፀም በመከታተልና በመቆጣጠርና ክፍተት ባሳዩ ስራዎች ላይ ድጋፍ ከማድረግ ባሻገር የአፈፃፀም እክል በታየባቸው ተግባራት ተቋማዊ የተጠያቂነት አሰራር ዘርግቷል። የከተማዋን አሁናዊ እድገት የሚመጥን የመልካም አስተዳደርና ቀልጣፋ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ከመፍጠርና ከመገንባት አንፃር ዘርፈ ብዙ ስራዎችን በመስራት ሂደት ውስጥ ምክር ቤቱ አይተኬ ሚነውን እየተወጣ ይገኛል።

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አሁን በደረሰበት 3ኛው ምዕራፍ ሁለተኛ ዓመት የስራ ዘመን ፍሬያማ ስራ እንዲሰራ ካስቻሉት ተግባራት ውስጥ በቋሚ ኮሚቴዎቹ የሚያደርጋቸው የተቋማት ድጋፍ ክትትልና ቁጥጥር አንዱ ተግባር ሲሆን ቋሚ ኮሚቴዎቹ ባደረጓቸው ወጥና ተከታታይነት ያላቸው የተቋማት አፈፃፀም የአካል ምልከታ የተቋማት የመፈፀም አቅም መላቅ፣ በከተማ አስተዳደሩ የሚገነቡ የግንባታ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም መሻሻልና በተቀመጠላቸው ጊዜና በጀት ማጠናቀቅ ማስቻል፣ የከተማውን የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ በመንገድ ግንባታ፣ የትምህርትና የጤና ሽፋንን በማሳደግ ረገድ የተገኙ አበረታች ውጤቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ምክር ቤቱ በበጎ ፈቃድ ተግባራት የከተማውን ነዋሪ የኑሮ ጫና ሙሉ በሙሉ መቅረፍ በሚያስችል ሁኔታ አንዳንድ በጣም የተቸገሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የከተማውን ነዋሪና ባለሀብት በማስተባበር የአረጋውያንና አቅመ ደካሞች ቤት በማደስና ፣ ማዕድ በማጋራት የኑሮ ጫናውን ለመቀነስ ከሚያደርገው ጥረት ባሻገር በከተማ ግብርና በሸገር ዳቦ ፣በሌማት ትሩፋት ፕሮግራሞች የሚሰሩ ስራዎች የነዚህን አቅመ ደካሞች ኑሮ የሚያግዝ፣ብሎም የሚያቀል እንዲሆን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በርካታ ስራዎችን ሰርቷል፡፡

በአዲሱ በጀት ዓመትም በ2015 የሰራናቸው ጠንካራ ስራዎችን በማስቀጠል ድክመቶቻችን በማረም ከመቼውም ጊዜ በላይ በርትተን መስራት ይጠይቀናል፡፡ እነዚህ በትኩረት ለማከናወን ያቀድናቸው ተግባራት ከግብ ለማድረስ ግን ዋናው አንድነታችን፣ ሰላማችን ነውና ሰላምን የሚያደፈርሱ አካላትን አጥብቀን በመታገል፣ ኅብረ ብሄራዊ አንድነታችንን በማጠናከር፣ ሰላማችንን በመጠበቅ ከከተማችን አልፎ የበለጸገች ኢትዮጵያ ለማየት ሁሉን አቀፍ ስራዎችን መስራት ይጠበቅብናል፡፡

በአዲሱ 2016 በጀት ዓመትም ያልተፈቱ ጥያቄውን እልባት በመስጠት የአገልግሎት አሰጣጣችንን በማዘመን በጋራ እንደ አንድ ቁመን የሕዝባችንን ፍላጎት የምናረጋግጥበት እንዲሆንልን እመኛለሁ፡፡

አመሰግናለሁ!

## የምክር ቤቱ 2015 ዓ.ም የተካሄዱ ጉባኤዎች ቅኝት

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በቻርተር አዋጅ 361/1995 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 2 አ መሰረት በየስድስት ወሩ የከተማ አስተዳደሩን አፈጻጸም ሪፖርት እንዲሁም ልዩ ልዩ አጀንዳዎችን መደበኛ ጉባኤ በማካሄድ ተወያይቶ ውሳኔ ያሳልፋል፡፡

በመሆኑም በ2015 በጀት ዓመት አራት መደበኛ ጉባኤዎችን በማካሄድ በከተማ አቀፍ ጉዳዮች ላይ መክሯል፡፡ የሕዝብ መብትና ጥቅም፣ ሰላምና ደህንነት እንዲሁም ልማት ለማረጋገጥ የተሰሩና እየተሰሩ ያሉ ተግባራትን አፈጻጸምን ገምግሟል፡፡ በአስፈጻሚ አካላት ሊተኮርባቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች ላይም አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

ለዚህም መነሻ ያደረገው የከተማ አስተዳደሩን የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በማዳመጥ ከተማ አስተዳደሩ  በበጀት ዓመቱ አፈጽመዋለሁ ብሎ በእቅዱ ከያዛቸው ግቦች አንጻር የተከናወኑ እና ያልተከናወኑ ተግባራትን በመለየት በዝርዝር ተወያይቶበታል፡፡ በሂደቱም የነበሩ ጥንካሬዎች እንዲቀጥሉ እጥረቶች ደግሞ ለቀጣዩ በጀት ዓመት እንደ ትኩረት አቅጣጫ ተይዘው ተፈጻሚ እነዲሆኑ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡





*የምክር ቤቱ 2ኛ ዓመት የስራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ጉባኤ ሲካሄድ*

በሌላ በኩል የህብረተሰቡን የፍትህ ተደራሽነት ከማረጋገጥ አንጻር በህግ ተርጓሚው በኩል እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን  የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤትን አፈጻጸም ሪፖርትን በስፋት  መገምገም ተችሏል፡፡ ፍርድ ቤቶቹ የፍትህ ስርዓቱ ሳይዛባ፣ ህግ ሳይጓደል ፍትሀዊ የሆነ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ የተከናወኑ ተግባራትን በዝርዝር ተመልክቶ ጠቃሚ እና የህዝብ ውግንናን ታሳቢ ያደረጉ ተግባራት እንዲጠናከሩ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከህብረተሰቡ የሚነሱ ጥያቄዎችንም ከመፍታተት አንጻር ተቋሙ በልዩ ትኩረት እንዲሰራ ማሳሰብ የተቻለበት ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም ሀገራዊውን የፍትህ ዘርፍ ሪፎርም አቅጣጫን በመከተል የከተማው የፍትህና የፖሊስ ተቋማት አሰራር ትራንስፎርሜሽን አቅጣጫ በማስቀመጥ፤ ሀገራዊውን የፍርድ ቤቶች ሪፎርም ፍኖተ-ካርታ ልምድ በመቀመር የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የህዝብን አመኔታ ያገኙ ተቋማት እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ሪፎርም ተልመው ሥራ ላይ እንዲያውሉ የማድረግ ስራዎችም በመልካም ጅምር ላይ ይገኛሉ፡፡





የምክር ቤቱ 2ኛ ዓመት የስራ ዘመን 3ኛ መደበኛ ጉባኤ ሲካሄድ

ከህግ አወጣጥና አተገባበር ክትትል አንጻርም፣ የምክር ቤቱን አሰራር ለስራ ዘመኑ ስትራቴጂክ ዕቅድ የሚመጥን ለማድረግ፣ የምክር ቤት ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ አሻሽሎ ከማጽደቅ ጀምሮ፣ ከከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ እና ከሌሎች አስፈጻሚ አካላት የቀረበለትን የህግ ይውጣልን ጥያቄዎች ተቀብሎ የከተማውን ነዋሪ መብትና ጥቅም የሚያስከብር መሆኑን በማረጋገጥ አምስት አዋጅና ስድስት ደንቦችን አጽድቋል፡፡

የሕዝብን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችሉ ተጨማሪ ተቋማትን አቋቁሟል፤ ለአገልግሎት አሰጣጥ እንዲያመችም መከፈል ያለባቸውን ተቋማት መልሶ አደራጅቷል፡፡ ካወጣቸው ህጎች አፈጻጸም ክትትል አኳያም፣ በወንጀል የተጠረጠሩ የምክር ቤት አባላትን ያለመከሰስ መብት ከማንሳት ጀምሮ ምክር ቤቱ ያወጣቸው ሕጎች በየደረጃው ተፈጻሚ መሆናቸውን በክትትል ቁጥጥርና ድጋፍ ጊዜ በቂ ትኩረት ሰጥቶ ተመልክቷል፤ ክፍተት ያለባቸውን የህግ ማዕቀፎች እንዲሻሻሉና አዳዲስ ህጎች እንዲወጡ በተገቢ ቦታ ምክረ ሀሳቦችን አቅርቧል፡፡





የምክር ቤቱ 2ኛ ዓመት የስራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባኤ ሲካሄድ

የዴሞክራሲ ስርዓት መርሆዎች አተገባበርና የግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓት ከመገንባት አንጻርም፣ የከተማው ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በኦዲት ያገኛቸው ግኝቶችን በማረምና በማስተካከል በኩል የሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶችን ለመድፈን የከተማውን ከፍተኛ አመራሮችና የፍትህ አካላትን ያሳተፈ የኦዲት ፎረም አደረጃጀት በመፍጠር፣ የመንግስትና የሕዝብ ሀብት ህግና አሰራርን በጠበቀ መልኩ ስራ ላይ እንዲውል የማድረግና ከአሰራር ውጭ የባከነ ሀብት ሲገኝ ተመላሽ የማስደረግ ስራን አከናውኗል፡፡



*በምክር ቤቱ መደበኛ ጉባኤ ላይ ረቂቅ አዋጅና የዋና ኦዲተር ሪፖርት ሲቀርብ*

ምክር ቤቱ በቀጣይ በጀት ዓመት ባለፈው ዓመት ተጀምረው ያልተጠናቀቁ ተግባራትን በማጠናቀቅ ረገድም በልዩ ትኩረት ይሰራል፡፡ በተለይ ተጠናቆ ስራ ላይ የዋለው የተቋማዊ አደረጃጀት ሪፎርም በከተማ ምክር ቤት ደረጃ ከፍተኛ መሻሻል ያመጣ ቢሆንም በክፍለ ከተማና በወረዳ ምክር ቤት ጽ/ቤቶች እየተነሱ ያሉ ተጨማሪ የማስተካከያ ጥያቄዎችን በጥናት ተመስርቶ ምላሽ እንዲያገኝ ማገዝ፤ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ሆኖ የተቋቋመው የመሬት ይዞታ ማስለቀቅና ካሳ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚ ጉባዔን ስራ ማስጀመር፤ ምክር ቤቱ የራሱን ሕንጻ ለመገንባት የተጀመረውን እንቅስቃሴ ወደ ተግባር የመቀየር፤ እየተሻሻለ ያለውን የምክር ቤት አሰራርና የአባላት ስነ ምግባር ደንብ በማጸደቅ በደንቡ የተመላከቱ ማሻሻያዎችንና ተጨማሪ አደረጃጀቶችን በፍጥነት ስራ ማስጀመር፤ የዳኝነትና የፍትህ አካላት ሪፎርም ዕቅድ ተከታትሎ ወደ ሙሉ ትግበራ ማሸጋገር፤ ምክር ቤቱ በበጀት ራሱን እንዲችል የተወሰደውን መልካም እርምጃ በሰው ኃይል አስተዳደር ረገድም ተፈጻሚ በማድረግ ከሌሎች መንግታዊ አካላት ጋር ያለውን ግኑኝነትና ገለልተኛ የተቆጣጣሪነት ስራ በሚዛናዊነት እያከናወነ በምርጫ ጊዜ በገባው ቃል ኪዳን መሰረት የከተማውን ነዋሪ መብትና ጥቅሞች ማስከበር የሚችል ተቋም ሆኖ በ2016 በጀት ዓመት አዳጊ ውጤቶች እንዲያስመዘግብ በትኩረት ይሰራል፡፡

የምክር ቤቱ አስተባባሪ ኮሚቴ በመደበኛ ስብሰባ ላይ

በተለይ በአስተባባሪ ኮሚቴው ሥራዎች እየተገመገሙ አቅጣጫዎች እንዲቀመጡ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አመራሩ ከከተማ እስከ ወረዳ ያለውን የምክር ቤት መዋቅር በተሻለ ሁኔታ አቀናጅቶና አደራጅቶ ይመራል፡፡ በተለይ ቋሚ ኮሚቴውና ሌሎችም የም/ቤቱ አደረጃጀቶች ተጠናክረው ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ከማድረግ አንፃር ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል፣ በቀጣይም ይሰራሉ፡፡ ተቋሙ ሀላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣም የመሪነት ሚናውን ሲጫወት ቆይቷል፡፡ በቀጣይም ይህ ተጠናክሮ ይቀጥላል፤ በተለይ መደበኛ የግንኙነት ጊዜን በመጠበቅ እየተገናኘ በልዩ ልዩ አጀንዳዎች ላይ አፋጣኝ ውሳኔ ከመስጠት አንጻር በጋራ በመገምገም በትኩረት ይሰራል፡፡

## የምክር ቤቱ የክትትልና ቁጥጥር ስራ

ከተማ አስተዳደሩ ለህብረተሰቡ ከአኗኗር ዘይቤውና ከፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አዳጊ ፍላጎቶቹ አንፃር ተቋማት የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች በሚፈለገው ደረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንደሆኑ ለማስቻል በሚያወጣቸው ፖሊሲዎችና ደንቦች በመታገዝ ይሰራል፡፡ ምክር ቤቶችም እነዚህ ተቋማት በእቅድ ከሚይዟቸው ተግባራት ጋር ተናበው ከመልካም አስተዳደር አንጻር ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥ መስፈኑን ለማረጋገጥ በሚያደርጓቸው የክትትልና ቁጥጥር አግባቦች የተቋማትን የአፈፃፀም ደረጃ በመስክ ምልከታ በመገምገም ለተሻሉ አፈፃፀሞች ይሁንታ በመስጠት ክፍተት አሉባቸው በሚባሉ አፈፃፀሞች ላይ ደግሞ የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫ በማስቀመጥ ለህብረተሰቡ የሚጠቅሙ ዘላቂ የልማት ስራዎች እንዲሰሩ የበኩላቸውን ሚና ይወጣሉ፡፡

በዚሁ መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤትም በከተማ አስተዳደሩ ማቋቋሚያ ቻርተር በአዋጅ ቁጥር 361/95 በተሰጠው ስልጣን ተግባርና ኃላፊነት መሰረት አስፈፃሚ አካላቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ይደግፋል፡፡

የክትትልና ቁጥጥር ስራውን የሚያከናውነው በስሩ በሚያቋቁማቸው ቋሚ ኮሚቴዎች አማካይነት ሲሆን ቋሚ ኮሚቴዎቹም ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጉባቸው መንገዶችም መሰረት የሚያደርጉት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በመገምገም ግብረ-መልስ በመስጠት እንዲሁም በሱፐርቪዥንና መስክ ምልከታ አማካኝነት ነው፡፡



*የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች*

በምክር ቤቱ ሰባቱ ቋሚ ኮሚቴዎች በስራቸው ከሰባት እስከ ዘጠኝ አባላት ያሏቸው ሲሆን እያንዳንዳቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በስራቸው ከስድስት እስከ አስር አስፈፃሚ ተቋማትን ይከታተላሉ፡፡ በተጨማሪም ቋሚ ኮሚቴዎቹ በተዋረድ የክ/ከተማ ዘርፍ ኮሚቴዎችን ይከታተላሉ፤ ይደግፋሉ፡፡






*ማዘጋጃቤታዊ ጉ/ቋ/ኮ የ2015 የተቋማት እቅድ ውይይት መድረክ*

የቋሚ ኮሚቴው ዓመታዊና የተከለሰ እቅድና አፈፃፀም ሪፖርት በየስድስት ወሩ ከኮሚቴው አባላት ጋር የጋራ በማድረግ በአስተባባሪ ኮሚቴ አስፀድቆ ወደ ስራ የሚገባ ሲሆን በዚህም መነሻነት ለሚከታተሏቸው አስፈጻሚ አካላትና ለዘርፍ ኮሚቴዎችም ግብረ መልስ በመስጠት የቀጣይ ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ መረጃ ቼክሊስት አካል በማድረግ የተጠናከረ እና ቀጣይነት ያለው ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡




*የመንግስት በጀት፣ ወጪና አስ/ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2015 የተቋማት እቅድ ውይይት መድረክ*

በትስስር አደረጃጀቶች የተደራጁ፣ ከመራጩ ህዝብ የቀረቡ ጥያቄዎች፣ በጉባኤ የም/ቤት አባላት የሚያቀርቧቸውን ጉዳዮች፣ በጥቆማና በቅሬታ ከህዝብ በቀጥታና ለምክር ቤቱ አፈ ጉባኤና ቋሚ ኮሚቴዎች የቀረቡ ጉዳዮች፣ ለም/ቤቱ በቀጥታ ተጠሪ ከሆኑ የዴሞክራሲ ተቋማት ማለትም ዋና ኦዲተር፣ አዲስ ሚዲያ ኔትወርክ፣ ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን፣ ከዳኝነት አካላት፣ የህዝብ አደረጃጀቶች እንዲሁም አንደኛው ለሌላኛው ቋሚ ኮሚቴ እና ከክፍለ ከተማና ከወረዳ ምክር ቤቶች በሚሰጡት ግብዓቶች ላይ በመመስረት ለክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ስራው በመረጃ ምንጭነት ይጠቀማሉ፡፡




*የንግድ፣ ኢንደስትሪና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2015 የተቋማት እቅድ ውይይት መድረክ*

በበጀት ዓመቱ ባከናወኗቸው ተግባራትም በአስፈፃሚ አካላትና በም/ቤቱ ያለውን ግንኙነት እና በህብረተሰቡ ዘንድም የምክር ቤቱን ተቀባይነት በማሳደግ ሂደት ጉልህ ሚና ተጫውተዋል፡፡

*የከተማ ልማት፣ ኮንስትራክሽንና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2015 የተቋማት እቅድ ውይይት መድረክ*

ይህም ምክር ቤቱ በህዝብ ዘንድ ያለውን ቅቡልነትና በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እድገትም በትክክል የአዲስ ምዕራፍ ምክር ቤትነቱን ተጨባጭ ለውጦች ማመላከት የተቻለበት ነው፡፡

*የሰላም፣ ፍትህና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2015 የተቋማት እቅድ ውይይትመድረክ*

ቋሚ ኮሚቴው ይህን አሰራር እስከታች ባለው መዋቅር በማውረድ ረገድ በመስክ ምልከታና ሱፐርቪዥን ስራዎች በተዋረድ ካሉ ኮሚቴዎቹ ጋር ተቀናጅቶና ተናቦ መስራቱም ውጤት የታየበት ነው፡፡




*የመሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2015 የተቋማት እቅድ ውይይት መድረክ*

በ2016 በጀት ዓመት በተቋማት ላይ ተገቢ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ፣ የግልፀኝነትና የተጠያቂነት አሰራር ስርዓትን ለማሳደግ ሰባቱም ቋሚ ኮሚቴዎች ከምክር ቤቱ መሪ እቅድ በመነሳት ገላጭና ነባራዊ ሁኔታዎችን መሰረት ያደረገ ዓመታዊ የስራ እቅድ ማዘጋጀት ችለዋል፡፡




*የሴቶችና ማህበራዊ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2015 የተቋማት እቅድ ውይይት መድረክ*

በዚህም መሰረት ለአርባ ሶስት አስፈጻሚ ተቋማት የ2014 በጀት አመት እቅድ አፈጻጸምና የ2015 እቅድ በመገምገም በተለይ የ2015 የተቋማት እቅድ በ2014 በጀት ዓመት ሳይከናወኑ የቀሩ ግቦች፤ ፕላን ኮሚሽን ካስቀመጣቸው ግቦች እና ከከተማው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ጋር የተናበቡ መሆናቸውን ተገምግሞ ወቅታዊና ጥራት ያለው ግብረ መልስ ተሰጥቷል፤

በሁሉም ሴክተር የተዘጋጁ እቅዶች የተቋሙን ተልዕኮ ማሳካት የሚችሉ፣ ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታን የዳሰሱ ስለመሆናቸው እና በተገቢው ሁኔታ የሚያሰሩ መሆናቸውን ከተረጋገጠ በኋላ ከአርባ ሶስቱ ሴክተር ተቋማት ጋር በዋና ዋና ግቦቻቸው ዙሪያ የስምምነት ሰነድ ፊርማ ተፈራርመዋል፡፡

## የቋሚ ኮሚቴዎችና የተቋማት የስምምነት ሰነድ ፊርማ







ቋሚ ኮሚቴዎቹ ከሚከታተሉዋቸው ተቋማት ጋር የስምምነት ፊርማ ሲፈራረሙ

የስምምነት ሰነድ ፊርማ መሰረታዊ ዓላማ ተቋማት በየዓመቱ የሚያቅዷቸውን ተግባራት የሚለኩ ወይም የሚቆጠሩ እንዲሆኑ ከማስቻሉ ባሻገር ምን ተግባር መቼ በምን ያህል በጀት እንደሚከናወን ማሳያም ጭምር ነው፡፡ በተለይ ደግሞ በክትትልና ቁጥጥር ሂደት አስፈጻሚውና ቋሚ ኮሚቴው መሀከል ተግባራቱን ቆጥሮ መስጠትና ቆጥሮ የመቀበል ባህል እንዲዳብር በማድረግ የክትትልና ቁጥጥር ሂደቱን ውጤታማ እንዲሆን ያግዛል፡፡





ቋሚ ኮሚቴዎቹ ከሚከታተሉዋቸው ተቋማት ጋር የስምምነት ፊርማ ሲፈራረሙ

ይህን የስምምነት ሰነድ መሰረት በማድረግ የየተቋማቱን የዕቅዳቸውን ዋና ዋና ግቦች መነሻ ያደረገ ተግባራትን በተለካና በተቆጠረ መንገድ ሊያሳይ የሚያስችል ቼክ-ሊስት በማዘጋጀት በዓመት በሁለት ዙር ሱፐርቪዥንና መስክ ምልከታ አካሂዷል፤



ቋሚ ኮሚቴዎቹ ከሚከታተሉዋቸው ተቋማት ጋር የስምምነት ፊርማ ሲፈራረሙ

በመሆኑም በስልጣንና ተግባራት ቅርርብ መሰረት በተደለደሉላቸው አስፈጻሚ አካላት ላይ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የተፈራረሙትን የዕቅዳቸውን ዋና ዋና ግቦች ስምምነት እና በየጊዜው በግቦቹ አፈጻጸም መሰረት በሰጡት ግብረ መልሶች መነሻነት የተቋማትን የአፈጻጸም ሪፖርቶች ተቀብለው የመገምገም ፣ በመስክ በመውረድ ስራቸውን የመፈተሽ እንዲሁም በዓመት ሁለት ጊዜ በሚደረግ ሱፐርቪዥን የክትትልና ቁጥጥር ድጋፍ ያደርጋሉ።



ቋሚ ኮሚቴዎች በሱፐርቪዥን ስራ ላይ

በሂደቱም፣ በተዋረድ የሚገኙ ምክር ቤቶችን የዘርፍ ኮሚቴዎች የማሳተፍ ተግባር በውጤታማነት ተከናውኗል። በዚህም መሰረት ሁሉም ቋሚ ኮሚቴዎች በበጀት ዓመቱ ለሰባ የዘርፍ ኮሚቴዎች ዕቅዳቸውንና የአራቱ ሩብ ዓመት አፈጻጸማቸውን በመገምገም የጽሑፍ ግብረ-መልስ ሰጥተዋል።




ቋሚ ኮሚቴዎች በሱፐርቪዥን ስራ ላይ

በሌላ በኩል ደግሞ ለአርባ ሶስቱ አስፈፃሚ ተቋማት የ2015 በጀት ዓመት የአራቱም ሩብ ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ተገምግሞ የፅሁፍ ግብረ-መልስ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፤ እንዲሁም በየጊዜው በግቦቹ አፈጻጸም መሰረት በቋሚ ኮሚቴው በተሰጡ ግብረ መልሶች መነሻነት የአፈጻጸም ሪፖርቶቻቸውን ተቀብለው በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት በመስክ በመውረድ ስራቸውን በመስክ ምልከታ እና በሱፐርቪዥን ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ አድርገዋል፡፡




ቋሚ ኮሚቴዎች በሱፐርቪዥን ስራ ላይ

በምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የመስክ ምልከታ የተለዩና ከአስፈጻሚ አካላት አቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ተለይተው በሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ እንዲፈቱ ማቅረብ ተችሏል፤ በዚህም ችግሮችም እየተፈቱ መጥተዋል፡፡ በሌላ በኩልም  የግልፀኝነትና የተጠያቂነት አሰራር በተሟላ አግባብና በጥራት ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የመልካም አስተዳደር የሌብነት እና ብልሹ አሰራር ማክሰሚያ እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ መግባቱን ቼክ ሊስት በማዘጋጀት  በክትትል የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም በምክር ቤቱ በተደረጉ ተከታታይነትና ወጥነት ባላቸው

የመስክ ምልከታና ሱፐርቪዥን ስራዎች በከተማ አስተዳደሩ ያሉ ተቋማት የአፈፃፀም ደረጃና ብቃት ማደጉን ማስተዋል ተችሏል፡፡



*የቋሚ ኮሚቴዎች የተቋማት ሱፐርቪዥን*

## የመንግስት በጀት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ



*የተከበሩ አቶ ጋትዌች ምር*

*የመንግስት በጀት ወጪና አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ*

ቋሚ ኮሚቴው አራት ተቋማትን የሚከታተል ሲሆን እነዚህም ዋና ኦዲተር ፋይናንስ ቢሮ ፣ገቢዎች ቢሮ ፣ የመንግስት ግዢ አገልግሎት እና የመንግስት ህንጻና ንብረት አስተዳደር ናቸው፡፡ ተቋማቱ የከተማዋ አጠቃላይ ሀብት የሚንቀሳቀስባቸው እንደመሆናቸው መጠን ወደ መንግስት መግባት ያለበት ገቢ በአግባቡ ስለመሰብሰቡ እንዲሁም የተበጀተው

**የመንግስት በጀት  አሰራርን ጠብቆ ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ በቋሚ ኮሚቴው ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡**



የመንግስት በጀት ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በመስክ ምልከታ ላይ

**በመሆኑም ኮሚቴው በበጀት ዓመቱ ይህ የህዝብ ሀብት በአግባቡ ለህዝብ አገልግሎት እንዲውል ከማድረግ አንጻር በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ በተለይ በሁሉም ዘርፍ የኦዲት ሽፋንና ተደራሽነት እንዲጠናከር በማድረግ የፋይናንስ ብሎም የሀብት አጠቃቀም ግልጸኝነትና የተጠያቂነት አሰራርን  ከማስፈን አንጻር ተጨባጭ ለውጥ ማስመዝገብ ተችሏል፡፡የቋሚ ኮሚቴው ትርፋማ የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ትርፋቸውን በመመሪያው መሰረት ፈሰስ እንዲያደርጉ እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሕግና ደንብን ተከትለው እንዲሰሩ ክትትል ማድረግ ተችሏል።**

## የንግድ ኢንዱስትሪ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ




*የተከበሩ ዶ/ር አቶሜ አበበ*
*የንግድ ኢንዱስትሪ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ*

የንግድ ኢንዱስትሪ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚከታተላቸዉ፤የሚደግፋቸዉና የሚቆጣጠራቸዉ የንግድ ቢሮ፣የስራ ኢንተርኘራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ፣ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ፣ የባህል ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ፣ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን እንዲሁም የክ/ከተማ ም/ቤት ዘርፍ ኮሚቴዎችን የበጀት ዓመቱን እቅድ እና አፈጻጸም በመገምገምና የማስተካከያ ግብረ-መልስ በአራት ዙር በመስጠት በእቅድ ተግባራትን እንዲያከናውኑ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው በበጀት ዓመቱ የህብረተሰቡን የኑሮ ውድነት ጫና ከመቀነስ አንጻር በተለይ የሸማች ህብረት ስራ ማህበራት ጋር ተያይዞ በመንግስት በድጎማ የሚቀርቡ ምርቶች አቅርቦትና ተደራሽነት ላይ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮች ላይ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት በክትትልና ቁጥጥር የታገዘ የማጥራት ስራ አከናውኗል፡፡ ይህን መነሻ ያደረገ ማስተካከያዎችም እንዲወሰዱ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ከስራ እድል ፈጠራ እንዲሁም ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስራዎች ጋር በተያያዘ በተለይ የስራ ፈላጊውን ወጣት ተጠቃሚነት ለማስፋት የተከናወኑ ስራዎችን በመፈተሽ አስፈላጊውን ድጋፍ አድርጓል፡፡





*የንግድ ኢንዱስትሪ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተቋማት የመስክ ምልከታ ላይ*

በተጨማሪም የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን መልሶ ከማቋቋም ፣ የሼዶች ፍትሀዊ ተደራሽነት ከማረጋገጥ ፣የከተማ ግብርና ስራዎች በሚፈለገው ደረጃ የተከናነወኑ ስለመሆናቸው ወርዶ ከማየት አንጻር ሰፋ ያሉ የክትትል ቁጥጥር እና ድጋፍ ተግባራትን አከናውኗል፡፡

## የከተማ ልማት፣ኮንስትራክሽንና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ



*የተከበሩ ወ/ሮ ነዒመተላህ ከበደ*

*የከተማ ልማትና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ*

የከተማ ልማትና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚከታተላቸውን ተቋማት ማለትም በቤቶች ልማት አስተዳደር ፣በዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ፣ከተማ ዉበትና አረንጓዴ ልማት እና አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ኮሚሽን ለበጀት ዓመቱ ያዘጋጁዋቸውን እቅዶች እና ሪፖርቶች በመፈተሽና ካለው ሀገራዊ እና ከተማ አቀፍ ሁኔታ አንጻር እንዲሆም የየተቋማቸውን ተልዕኮ በማሳካት ስለመቻላቸው የማረጋገጥና ግብረ መልስ የመስጠት ተግባራትን በአራት ዙር አከናውኗል።

በክትትልና ቁጥጥር ሂደቱ የካፒታል ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ፣ጥራት እና ዋጋ መሠረት እንዲከናወኑ፣ከ20/80 እና በ40/60 ፕሮግራም የተገነቡ ከሀያ አምስት ሺ በላይ ቤቶች በዕጣ በማስተላለፍ ውል የማዋዋል ስራ መከናወኑን ኮሚቴው በክትትል ሂደቱ በጥንካሬ አይቷል። ለኪራይ የተገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በማስተላለፍና በማስተዳደር ረገድ ያሉ ክፍተቶች መቅረፍ የሚያስችል እና የጋራ መኖሪያ ቤቶች ኪራይ ተመን ዋጋ ጥናት መከናወኑ እና የመንግስት ገቢ ከፍ እንዲል መደረጉ፣ለመንግስት ሰራተኞች የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ፋይናንስ ማመቻቸት መቻሉ፣ለጋራ ህንፃ መኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት 30% ብድር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲመቻች መደረጉ ፣በቤት ህብረት ስራ

ማህበር ለመደራጀት ጥያቄ ያቀረቡና መሰፈርቱን ያሟሉ ተመዝጋቢዎች መደራጀታቸው እና የቤት ፍላጎት ጫናን መቀነሱ በእቅድ ተይዘው መሳካት ከቻሉ ተግባራት ተጠቃሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ ችሏል።




*የከተማ ልማትና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተቋማት መስክ ምልከታ ላይ*

በሌላ በኩል በመዋቅራዊ ፕላኑ ለአረንጓዴ ልማት የተመለከቱ ቦታዎች የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ለማውጣት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ለማስጨረስ የተደረገ ጥረት ቢኖርም በሚፈለገው መልኩ አለመሆኑ፤አንዳንድ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ማጠናቀቅ አለመቻል፤ፕሮጀክቶች ወደ አካባቢ ጥበቃ መጥተው እንዲገመገሙ ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ትስስር አለመፍጠር፣ በከተማዋ ነባር ተቋማት የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ እንዲያቀርቡ ተደራሽ አለመሆን እና ለኢነርጂ ቴክኖሎጂ ማሻሻል የሚረዳ ወርክሾፕን ወደ ሥራ እንዲገባ አለማድረግ ደግሞ በእቅድ ተይዘው ሳይፈቱ የቀሩ ቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች መሆናቸውን ማየት ተችሏል። በመሆኑም ቋሚ ኮሚቴው በዚህ በጀት አመት ያልተከናወኑ ተግባራት በቀጣይ 2016 በጀት አመት እቅድ ላይ በማካተት የህዝቡን የመልካም አስተዳደር እና የልማት ጥያቄዎችን ምላሽ በመስጠት  የህብረተሰቡን እርካታ ለማሳደግ ይሰራል።

# የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ




*የተከበሩ አቶ ማሾ ኦላና*

*የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ*

የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚከታተላቸው ተቋማት ፕላንና ልማት ኮሚሽን፣ የመሬት ልማት እና አስተዳደር ቢሮ፤ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ እንዲሁም የዋና ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ሲሆኑ የተቋማቱን የበጀት ዓመቱን እቅድና ሪፖርታቸውን በመገምገም የፅሁፍ ግብረ-መልስ እንዲደርሳቸው የተደረገ ሲሆን፤ ኮሚቴው በበጀት ዓመቱ በሁለት ዙር መስክ ምልከታና ሱፐርቪዥን በክትትልና ቁጥጥር ስራው የነበሩ ጠንካራ ጎኖችን በማስቀጠልና እጥረቶችን ደግሞ ቀርፎ በመሄድ ረገድ አበረታች ተግባራትን አስመዝግቧል፡፡

በዚህም መሰረት  በዋና ስራ አሰኪያጅ ጽ/ቤት ስር ተጠሪ በሆኑ ተቋማት በተለይ በወሳኝ ኩነት ፣ደረቅ ቆሻሻ እንዲሁም ሌሎች የተሻለ አገልግሎቶች እንዲሰጡ የተጀመሩ መልካም ስራዎች

አበረታች መሆናቸው ታይቷል፡፡ በተለይ ከመታወቂያ አገልግሎት ጋር ተያይዞ ያለው ችግር በዘለቄታዊ መንገድ መፍታት መቻሉ፣ ከእሳትና ድንገተኛ አደጋ ጋር ተያይዞ በዋናነት የአደጋ ቅድመ መከላከል በትኩረት እንዲሰራ ውጤታማ ድጋፍ ተደርጓል፡፡




የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተቋማት መስክ ምልከታ ላይ

ከመሬት እና መሬት ነክ ከሆኑ አገልግሎቶች ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የተቋም ግንባታ ስራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል አገልግሎት አሰጣጥን በማዘመን ላይ በትኩረት እንዲሰራ ኮሚቴው በክትትል ሂደቱ አመላክቷል፡፡

በተጨማሪም የተጠያቂነት አሰራር ስርዓትን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር በተለይ ከመሬት ወረራ ጋር ተያይዞ እየታዩ ያሉ ችግሮችን የተለዩ አሰራሮችን በመዘርጋት መቅረፍ እንደሚገባ ቋሚ ኮሚቴው አቅጣጫ ከሰጠባቸው ተግባራት መካከል ይገኙበታል፡፡

## የመሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ



የተከበሩ ወ/ሮ ልዕልት ግደይ
የመሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ

የመሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በጠቅላላው ስድስት ተቋማትን የሚከታተል ሲሆን እነዚህም ትራንስፖርት ቢሮ ፣ውሃና ፋሳሽ ባለስልጣን፣ኤሌክትሪክ አገልግሎት ቢሮ፣ መንገዶች ባለስልጣን፣ የግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን እና ህብተረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ናቸው፡፡

ቋሚ ኮሚቴው እነዚህ የመሰረተ ልማት ገንቢ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከነዋሪው የእለት ተዕለት የአገልግሎት ፍጆታ ጋር የተቆራኙ እንደመሆናቸው መጠን የክትትልና ቁጥጥር ሂደቱን በልዩ ትኩረት አከናውኗል፡፡ በተለይ በበጀት ዓመቱ ግብ አስቀምጠው በረጅም፣ መካከለኛና አጭር ጊዜ ለመከወን ያለሟቸውን ተግባራት በትኩረት የመገምገም ስራው በጥልቀት የተሄደበት ነው፡፡ በተለይ የመንገድ እና የውሃ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ ቅንጅታዊ አሰራር መፍጠርና የከተማ አስተዳደሩን ዘላቂ የመሰረተ ልማት አቅርቦት መፍጠር በክትትል ሂደቱ በትኩረት አቅጣጫ የተቀመጠ ነጥብ ነበር፡፡

የኤሌክትሪክ ሀይል መቆራረጥና በመንገድ ላይ ለአደጋ ከሚያጋልጡ ፖሎች ጋር ተይይዞ የተከሰቱ ችግሮችን በልዩ ውሳኔ እንዲፈቱ ከማድረግ አንጻር ኮሚቴው አበረታተች ድጋፍ አድርጓል፡፡ እንዲሁም በትራንስፖርት ዘርፍ በየቀኑ የሚጓጓዘው የትራንስፖርት ተጠቃሚ ህዝብ በታቀደው ልክ አፈፃፀሙን ማሳደግ ላይም በተመሳሳይ ጠንካራ ድጋፍና ክትትል አድረጓል፡፡በሌላ በኩል የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎፈቃድ ስራን ከማጠናከር አንጻር መልካም የሆነውን የመረዳዳት እሴት ይበልጥ በማጠናከር እየተሰራ ስለመሆኑ ኮሚቴው በትኩረት ከዳሰሳቸው መሀከል ይገኙበታል፡፡





የመሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተቋማት መስክ ምልከታ

ቋሚ ኮሚቴው በቀጣይ 2016 በጀት ዓመት የቅድመ ዝግጅት ተግባራትን በተጠናከረ አግባብ በማከናወን እና ካለፈው ዓመት የተሻለ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለቀጣይ በጀት ዓመት ዕቅድ ስኬት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ቀዳሚ ተግባሩ በማድረግ ይሰራል፡፡

## የሴቶችና ማህበራዊ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ




የተከበሩ ወ/ሮ ዘይነባ ሽኩር

የሴቶችና ማህበራዊ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ

የሴቶችና ማህበራዊ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በ2015 በጀት ዓመት ከዘርፍ ኮሚቴዎች ጋር በመቀናጀት ክትትልና ቁጥጥር በሚያደርግባቸው ሴክተር መስሪያ ቤቶች የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ ትምህርት ቢሮ፤ ጤና ቢሮ፣ ሴቶችና ማህበራዊ ልማት ቢሮ፣ ኮሙኒኬሽን ቢሮ፤ ትምህርት ስልጠና ጥራትና ሙያ ብቃት ማረጋገጥ፣ በምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን፣ ምገባ ኤጀንሲ፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እና በትምህርት አመራር አካዳሚ እና በስራቸው ባሉ ተጠሪ ተቋማት ላይ ውጤታማ የክትትልና ቁጥጥር ስራ አከናውኗል፡፡

በጤናው ዘርፍ ያለውን  አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማ ከማድረግ አንጻር የጤና ተቋማት በበቂ የሰው ሀይል ግብዓት ተሟልተው አገልግሎት እንዲሰጡ ከማድረግ ጎን ለጎን በቅድመ መከላከል ስራው ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ከትምህርት ጥራትና ተደራሽነት ጋር ፣ በአስተሳሰብ የተለወጠ በሀገራዊ አጀንዳ ላይ የሳፋ ግንዛቤ ያለው ተተኪ ወጣት ከመቅረጽ አንጻር ተቋማቱ ያከናወኑዋቸውን ተግባራት በጥልቀት ገምግሞ ድጋፍ አድርጓል፡፡

የሴቶችና ማህበራዊ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በተቋማት መስክ ምልከታ ላይ

በተመሳሳይ ሁሉም ተቋማት በተሰጣቸው ተልዕኮ መሰረት  ሃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ  ከማስቻል አንጻር ቋሚ ኮሚቴው ሰፋ ያለ ክትትል ቁጥጥርና ድጋፍ አድርጓል፡፡ በቀጣይ በጀት ዓመት የማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ የከተማው ነዋሪ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች የሚመልስና እርካታ የሚጨምር እቅድ አፈፃፀም እንዲኖር የተቀናጀና የተጠናከረ ክትትል ድጋፍና ቁጥጥር ቋሚ ኮሚቴው ያካሂዳል፡


## የሰላም፣ የፍትህና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ



የተከበሩ አቶ ሙሉነህ ደሳለኝ
የሰላም፣ የፍትህና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ

የሰላም፣ የፍትህና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አስር የሚደርሱ ተቋማትን የሚከታተል ሲሆን ተቋማቱ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ፣ከንቲባ ጽ/ቤት፣ምክር ቤት ጽ/ቤት፣ፍትህ ቢሮ፣ፍርድ ቤቶች እና ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ ፣ፖሊስ ኮሚሽን እና ደንብ ማስከበር ኤጀንሲ ይገኙበታል፤  በበጀት ዓመቱ ተቋማቱ ያቀዱዋቸውን እቅዶች በጥልቀት መርምሮ ግብረ መልስ መስጠትና ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው እነዚህን አስፈጻሚ እና ህግ ተርጓሚ ተቋማት ከማእከል እስከ ወረዳ ባለው መዋቅራቸው ወርዶ በመመልከት በአፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችን በመለየት እና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በመጠቆም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ውጤታማ የድጋፍና ክትትል ስራ አከናውኗል።




የሰላም፣ የፍትህና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በመስክ ምልከታ ላይ

በተለይ በከተማ ክለሳ የተደረገበት የመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናት የሚያካሂዱ ተቋማት ላይ የሰራተኞች የድልድል መመሪያ ቁጥር 136/2015 መሰረት በማእከል፣ ክፍለ ከተማና ወረዳ በአግባቡ እንዲጠናቀቅ ቋሚ ኮሚቴው በተቋሙ ሁለ ገብ የሆነ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ማድረጉ እና የከተማዋን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ህብረተሰቡ ባለቤትና ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ቋሚ ኮሚቴው ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፤ይህም በከተማችን አለም አቀፍና አህጉራዊ መድረኮችን፣ ልዩ ልዩ አገር አቀፍ ሁነቶችን፣ በዓላት፣ እንደማዘጋጀቷ ያለምንም የጸጥታ ችግር እንዲከናወኑ ማድረግ ያስቻለ ነበር።

በቀጣይ በጀት ዓመት በቋሚ ኮሚቴው በየተቋማቱ ታቅደው ያልተከናወኑ ተግባራት መኖራቸውን በመገምገም በቀጣይ ዓመት በቅድሚያ ሊከናወኑ የሚገባቸውን እቅዶች በመለየት የሚሰሩ ስራዎች ላይ ከወዲሁ በቂ ዝግጅት እያደረገ ይገኛል።

/

# የምክር ቤት ጽ/ቤቱ የበጀት ዓመቱ የስራ እንቅስቃሴ ቅኝት



አቶ አብዲ ፀጋዬ
የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽ/ቤት ኃላፊ

የም/ቤት ጽ/ቤቱ በቻርተር አዋጁ መሰረት በአዋጅ ቁጥር 34/2004ን በነባሩ አዋጅ የነበሩ ክፍተቶችን ሊሞላ በሚችል መልኩ ተሻሽሎ አዋጅ ቁጥር 80/2015 ተብሎ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ ጽ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት የአስተባባሪ ኮሚቴ አባል የሆነና ለአፈ ጉባኤ ተጠሪ የሆነ፤ ለም/ቤቱ ሙያዊና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን የሚያቀርብ፣ በስሩ ያሉ የስራ ክፍሎችን/ዳይሬክቶሬቶችን እና ፈፃሚዎችን እንዲሁም በተዋረድ ያሉ የክ/ከተማና ወረዳ ምክር ቤቶች ጽ/ቤቶች የሚደግፍ ነው፡፡

ጽ/ቤቱ በአግባቡ ለምክር ቤቱ የሚጠበቅበትን ሙያዊና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ማቅረብ እንዲችል ተደርጎ ሪፎርም የተደረገ ሲሆን፣ አራቱ ሙያዊ ድጋፍ ሰጪ የሥራ ክፍሎች በሜሪት ተሿሚ እንዲመሩ የተደረገለት እንዲሁም በበጀትና በሰው ሃይል ስምሪት ነጻ ሆኖ ስራውን እንዲያከናውን የተደረገ እንደመሆኑ፣ ካለፈው ጊዜ በተሻለ ቁመና ላይ ይገኛል፡፡



የጽ/ቤቱ ሰራተኞች በድልድል መመሪያ ስልጠና ላይ ሲወያዩ

በዚህም መሰረት ጽ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ አበረታች ክንውኖችን ያለውን በጀትና እጥረቱን የሚሞላ ረቂቅ በጀት በማዘጋጀት ተጨማሪ በጀት 8 ሚሊዮን እንዲፈቀድ የተሻለ ሙያዊ ድጋፍ መስጠት መቻሉ፣ ያለውን በጀት ለታለመለት ዓላማ በማዋልም የተደረገ ጥረት፣ የተጀመረውን የጽ/ቤት ሪፎርም በማጠናቀቅ የሰው ኃይል ድልድል ማድረጉ፣ ለክ/ከተማና ወረዳ ጽ/ቤቶች በሱፐርቪዝን የታገዘ ድጋፍ ማድረግ መቻሉ፣ የጊዜ መዘግየት ቢኖርም የቢሮ ግብዓቶችን ለማሟላት የተደረገ ጥረት፣ የ2016 ረቂቅ በጀትን በተሻለ መነሻና ማስረጃ አዘጋጅቶ ለም/ቤት አመራሩ በማቅረብ በሚመለከታቸው አካላት ባለፈው ዓመት ከነተጨማሪው በጀት ከነበረ 112 ሚሊዮን ብር 170 ሚሊየን ማድረስ መቻሉ ዋና በጥንካሬ የተነሱ ተግባራት መካከል ዋናዎቹ ማሳያዎች ናቸው፡፡



የጽ/ቤቱ ሰራተኞች በአቅም ግንባታ ስልጠና ላይ የሚያሳይ ፎቶ

ይሁን እንጂ፣ ጽ/ቤቱ በአዲሱ የተቋማዊ አደረጃጀት ጥናት ከተፈቀዱለት የሥራ መደቦች መካከል ቁልፍ የሆኑትን የህግ ዝግጅት ሙያዊ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ጨምሮ በርካታ የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፣ ተዋዳዳሪ ባላለፉባቸው አንዳንድ ዓላማ ፈጻሚ ሥራ መደቦች (በተለይ ክትትልና ቁጥጥር) ከውስጥ የተመደቡ ነባር ባለሙያዎች በታቀደው ልክ የሪፎርሙን ዓላማ ላያሳኩ ይችላሉ የሚል ስጋት መኖሩ፣ እንደ ህግ ዝግጅት ያሉ የስራ መደቦች

የተፈቀደላቸው ደረጃ ብቁ ባለሙያዎችን ከገበያ ለመሳብ የማያስችል መሆኑ፣ በተዋረድ በሚገኙ የምክር ቤት ጽ/ቤቶችም ከተፈቀደላቸው ደረጃ ዝቅ ማለት ጋር ተያይዞ በቂ የሰው ኃይል ያለመገኘት ችግር ቀጣይ ትኩረትና ለምክር ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተጨማሪ ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች ናቸው፡፡

## *ትስስር አደረጃጀት የስራ እንቅስቃሴ*

የሕዝብ ውክልና የምክር ቤቱ አንዱ ዋነኛ ተልዕኮ እንደመሆኑ መጠን፣ የሕዝብ እንደራሴዎቹ ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር በየጊዜው እየተገናኙ እንዲወያዩ ለማስቻል የተፈጠሩ የሕዝብ ተመራጮች ትስስር አደረጃጀቶች ካለፈው በጀት ዓመት የወሰዳቸውን ልምዶች በማጠናከር በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ በዋናነትም፣ በሕብረተሰብ ተሳትፎ የሚሰሩ የልማት ስራዎችን ሕዝብ በማነቃነቅ፣ ፋይናንስ በማፈላለግ፣ ከማገዝ በተጨማሪ፣ በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ፣ በማዕድ ማጋራት፣ በአቅመ ደካሞች ቤት ዕድሳት፣ በአረንጓዴ አሻራ ተመራጩንና መራጩን ሕዝብ የማነቃነቅ፣ በአርአያነትም የማሳተፍ አሻራ ያለው ስራ ሰርቷል፡፡




የትስስር አደረጃጀት አባላት በበጎ ፈቃድ ስራ ላይ

የም/ቤት አባላት የወከላቸውን ህዝብ ጥያቄና በምርጫ ወቅት ቃል በገቡት መሰረት አደራቸውን ለመወጣት የሚያስችላቸውን መመሪያ በማዘጋጀት በም/ቤት አባላትም ሆነ በመራጩ ህዝብና የአገልግሎት ማዕከል የሆኑት አስፈፃሚ የመንግስት አካላት ላይ ሰፊ የንቅናቄና የግንዛቤ መድረኮችን በማዘጋጀት ጥሩ መግባባት የተደረሰበት ሲሆን ከከተማ

እስከ ወረዳ ወጥ የሆነ የስራ ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ተነድፎ ተግባራዊ መደረጉ ይታወቃል፡፡




*የትስስር አደረጃጀት የውይይት መድረክ*

በመሆኑም የትስስር አደረጃጀቶቹ ከከተማ እስከ ወረዳና ቀጠና ድርስ በተፈጠረው ንቅናቄ ልክ የጋራ መግባባት ተፈጥሮ ወደ ስራ በመግባታቸው፣ በተለይም የክ/ከተማና የወረዳ ም/ቤት አባላት በነበረው የቡድን አደረጃጀት በበጎ ተሞክሮነትና ለትስስሩ አደረጃጀት እንደ ግብዓት በመጠቀም ኃላፊነትን ለመወጣት የተፈጠረው ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ለውጡን በማረጋገጥ አወንታዊ ተግባራት ተከናውኗል፡፡




*የትስስር አደረጃጀት የውይይት መድረክ*

የመራጭ ተመራጭ ግንኙነት ስራ ባለፉት የም/ቤት የስራ ዘመናት ትኩረት ተሰጥቶት አሰራር ያልተዘረጋለትና ቅድሚያ ተሰጥቶ የአሰራር መመሪያ ሰነድ እንዲዘጋጅ የአቻ

ም/ቤቶችን ተሞክሮና የውጭ ሀገራትንም ልምድ በመውሰድ የመመሪያ እንዲዘጋጅ መደርጉ ይታወሳል፡፡

ወጥ የሆነና ተመሳሳይ ስራዎችን በተለያየ የም/ቤት አደረጃጀት ይሰሩ የነበሩትን ድግግሞሽን በማስወገድ አንዱ የም/ቤት እርከን ከሌላው ተናቦና ተቀናጅቶ የሚሰራበት የህዝብ ተመራጮች ትስስር አደረጃጀት የአሰራር መመሪያ በተዘጋጀው መሰረት የከተማ ም/ቤት አባላት በየተመረጡበት ክ/ከተማ የትስስር አደረጃጀት እንዲደራጁና አመራር ኮሚቴዎቻቸውን እንዲመርጡ ተደርጓል፡፡



የመራጭ ተመራጭ ትስስር አደረጃጀት በክ/ከተሞች ቢሮ ርክክብ ሲያደርግ

ከቀጠና እስከ ክ/ከተማ በሁሉም እርከን የትስስር አደረጃጀቶች የአመራር ኮሚቴ መደራጀቱን የማረጋገጥ ስራ ተሰርቶ በሁሉም ክ/ከተሞች በተቀመጠለት አቅጣጫና አሰራር እንዲከናወን መደረጉና የክ/ከተማ ትስስር አደረጃጀቶች ቢሮና ደጋፊ ባለሙያም ተሟልቶላቸው የከተማ ም/ቤት አፈ ጉባኤና ም/አፈጉባኤ፣ የክ/ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚዎችና አፈ ጉባኤዎች በቦታው ተግኝተው በይፋ ተጀምሯል፡፡ በዚህም ማህበረሰቡን በማንቀሳቀስ የተለያዩ የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎችን ለመስራት የተሄደበት ርቀት የተሻለ ነው፡፡

በአላትን በማስመልከት እንዲሁም በመደበኛነት በህዝባዊ አደረጃጀት በመሳተፍ የስጋት ቦታዎችን መለየት ህገ ወጥነትን በመከላከል በቅንጅት በመስራት የትስስር አደረጃጀቱ አመርቂ ስራ ሰርተዋል፡፡




*የትስሰር አደረጃጀት አባላት በበጎፈቃድ ስራ ላይ*

የአካባቢ ፅዳት የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ አስፈላጊ መሆኑን በቂ ግንዛቤ መያዙ፤ ክፍለ ከተማን ጨምሮ ሁሉም የትስስር አደረጃጀት የፅዳት ዘመቻ ስራ ላይ ከፍተኛ ርብርብ ማድረጋቸውና ቆሻሻ ሀብት መሆኑን መገንዘባቸውና በዚሁ ስራ ላይ በርካታ የትስስር አደረጃጀት አባላት ተጠቃሚ መሆናቸው እንዲሁም በፅዳት ዘመቻ ወቅት በየቀጣናቸው ግንባር ቀደም ሆነው በንቅናቄው ላይ መሳተፋቸው ታይቷዋል፡፡





የህብረተሰብ የበጎ ፍቃድ የፅዳት ተሳትፎ

በተጨማሪ እንደ ምክር ቤት የቤት እድሳት ተግባር ከቀን ወደ ቀን እየተሻሻለ እና ልምድ እየተወሰደበት የመጣ ሲሆን በዚህ በጀት አመትም ከወረዳ ምክር ቤቶችና ከባለ ሃብቶች እንዲሁም ከግብረ ሰናይ ድረጅቶች ጋር በመግባባት ከአምናው በተሻለ በርካታ አቅመ ደካሞችን ቤት ማደስ ተችለዋል፡፡





*የትስስር አደረጃጀቱ ቤት እድሳት ስራዎች*

***የም/ቤት አመራሩና የትስስር አደረጃጀት አመራር ኮሚቴው በክ/ከተማና በወረዳ በቡድን አደረጃጀት ታቅደው በስራ ላይ የነበሩ መልካም ተግባራትን በትስስር አደረጃጀቱ ለውጡን በተግባር በማረጋገጥ ጥሩ አቅም መፍጠር ተችሏል፡፡ ክ/ከተሞች ለመድረኩ የተለየ ዝግጅትና ትኩረት ሰጥቶ ውጤታማ በማድረግ በአስፈፃሚና ም/ቤት መናበብና ቅንጅት፣ጥሩ መነሳሳት ታይቷል፡፡***

***በዚህ በጀት ዓመትም የትስስር አደረጃጀቱ ያከናወናቸው በውጤት የታጀቡ በርካታ ተግባራት እንዲከናወኑ በማድረግ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል፡፡ለዚህም ምክር ቤቱ በየደረጃው እውቅና ሰጥቷቸዋል፡፡***






*የትስስር አደረጃጀት እውቅና መድረክ*

***በመሆኑም በከተማችን በለውጥ አመራሩ የተያዙ ዕቅዶችን ወደ ተግባር ለመቀየር በምክር ቤቱ ያሉ አደረጃጀቶች ጠንካራ ተቋም እንዲሆኑና የተደራጀ እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው ማድረግና በየደረጃው በአገልግሎት አሰጣጥ በልማት የህብረተሰባችንን ፀጥታ በመጠበቅ በተለያዩ የበጎ ፍቃድ ተግባራት በመሳተፍ የኑሮ ውድነትን ለማርገብ ወጣቶችን እና ሴቶችን የሥራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የከተማ ግብርናን በማጠናከር የጓሮ አትክልት ልማት ስራን (የሌማት ትሩፋት) በተለየ ትኩረት በመስጠት በዚህ ሂደትም ያሉ***

**ችግሮች እንዲፈቱ በሚደረገው የትስስር አደረጃጀት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡**



የአካባቢ ልማትና ማህበራዊ ተሳትፎ ስራዎች

አሮጌ ሊባል ቀናት በቀሩት 2015 ዓ.ም በሰው ተኮር ስራዎች ህዝቡንና ባለሀብቱን በማስተባበር ውጤታማ ስራ መስራት ተችሏል። የአዲስ አበባ ከተማ ምክርቤት ህብረተሰቡን በማስተባበር በጎ ፍቃደኝነትን ባህል ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶት እየተሰራ ነው።

**እነዚህ በጎ ስራዎችን ይበል የሚያሰኙና ቀጣይነት እንዲኖረው የሁላችን ድርሻ መሆን አለበት እያልን ቅኝታችን እዚሁ እናብቃ ሰላም!**

## ሴት የምክርቤት አባላት ኮከስ የስራ እንቅስቃሴ

3ኛው ዙር የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት 58 ያክል ሴት አባላት አሉት፡፡ ከነዚህ ሴቶች አብዛኛዎቹ በተለያየ ደረጃ በአመራርነት እና በኃላፊነት ላይ ያሉ ናቸው፡፡








ሴት የምክር ቤት አባላት ኮከስ የውይይት መድረክ

ኮከሱ በዋናነት ሴት የም/ቤት አባላት ሴቶችን በተለየ የሚመለከቱ ጉዳዮችን ማዕከል በማድረግ በተደራጀ ሁኔታ እንዲወያዩ፤ በምክር ቤት በሚወጡ ህጎችና ፖሊሲዎች መብትና ጥቅሞቻቸው መከበራቸውን፤ በአስፈጻሚ አካላት ላይ በሚደረጉ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችም የሴቶች እኩልነት፣ መብትና ጥቅም ጉዳዮች ትኩረት እንዲያገኙ በተደራጀ ሁኔታ ለመምከር፣ ለመታገልና ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መልኩ ተጽዕኖ ሊያደርጉ የሚችሉ አደረጃጀትና አሰራሮችን ለማስቀረት የሚሰራ እንደመሆኑ፣ ለዚሁ አጋዥ የሆኑ ኃይላትንና ሀብትን በማሰባሰብ የመስራት ጅምር ስራዎች ቢኖሩም፤ ለአባላቱ በተለያዩ ጉዳዮች ግንዛቤ ለመፍጠርና

አቅማቸውን ለመገንባት ከተሰሩት ስራዎች ባሻገር ወቅቱን ጠብቆና በተሟላ አቅም ወደ ተግባር ከመግባት አንጻር ውስንነት ያለበት መሆኑ ለቀጣይ እቅድ እንደ ትኩረት መነሻ ተወስዷል፡፡

## ብሔራዊ ባዓላት አከባበር

በኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔራዊ በዓላት ይከበራሉ፤ ከነዚህ ውስጥም ሰንደቅ ዓላማ ቀን እና የኢትዮጵያ ብሄርብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን ተጠቃሽ ናቸው፡፡

### ሰንደቅ ዓላማ

ሰንደቅ ዓላማ የሚለው ቃል የአንድ ሀገር መለያ ምልክት መታወቂያ የህዝቦች የአንድነት መጠበቂያ እንዲሁም የአንድ ሀገርና ህዝብ የማንነት መለያ ምልክት መሆኑን የሚያመላክት ቃል ነው፡፡ ሰንደቅ ዓላማ ከምልክትም በላይ ነው፡፡




የሰንደቅ ዓላማ ቀን በከተማ ደረጃ

የኢትዮጵያ የሰንደቅ ዓላማ ሀገርና ህዝብን በመወከል ከባለታሪኮቹ የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር አብሮ ተጉዟል፡፡ በዚህም የሰንደቅ ዓላማ ታሪክ ካላቸው ሀገራት መካከል ቀዳሚ ቦታ የምትይዝ ሀገር ሆናለች፡፡ ከ1880ዎች ሁለተኛ አጋማሽ ድረስ አንድ ወጥ እንዳልነበረና፤ በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ሰንደቅ ዓላማ ልዩ ትርጉም የተሰጠው 1898 ዓ.ም እንደነበረ ታሪክ ይነግራል፡፡ በዚህ ጊዜ በተሰጠው ትርጓሜ መሰረት ቢጫ ብርሃን፤ ቀይ የመስዋዕትነት፤ አረንጓዴ የተስፋ ምልክት ተደርጎ እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡

ከዚህ በኋላ የኢፌዲሪ የሰንደቅ ዓላማ ህግ አዋጅ ቁጥር 654/2001 አንቀጽ 5 የሪፐብሊክ ሉዓላዊነትና የኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በፍላጎትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ የአንድነታችን መገለጫ ምልክታችን ሆኖ እንዲያገለግል ሆኗል፡፡ የብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀንም በአዋጅ ቁጥር 863/2006 አንቀጽ 2 በየዓመቱ ጥቅምት ወር በገባ መጀመሪያ ሳምንት ሰኞ እንዲከበር ተደንግጓል፡፡

*የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት  አመራሮችና ሰራተኞች የሰንደቅ አላማ ቀን  ሲያከብሩ*

በዚህ መሰረት ባለፉት 14 ዓመት ሰንደቅ አላማ በፌዴራል፤ በክልልና በሁለቱም ከተማ አስተዳደሮች ደረጃ ስለ ሰንደቅ ዓላማ ምንነት፤ የተለያዩ መልዕክቶችን በማስተላለፍ፤ የሰንደቅ ዓላማ መስቀል ስርዓት በማከናወን ሲከበር ቆይቷል፡፡

በዘንድሮ ዓመትም ጥቅምት 7/2015 ዓ.ም የ15ኛው የሰንደቅ ዓላማ ቀን ‹‹የሰንደቅ ዓላማችን የብዝሃነታችን መገለጫ የሉዓላዊነታችን ምሶሶ ነው!›› በሚል መሪ ቃል በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል፡፡ በኢ.ፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 3 ላይ ብሂራዊ ሰንደቅ ዓላማ ብዝሃነትን የሚወክሉ እሴቶችና ትርጓሜዎች እንዳሉ በግልጽ የደነገገ በመሆኑ መንግስትም ይህንኑ ተከትሎ ዜጎች በሰንደቅ ዓላማ ቅርጽና ትርጓሜ ላይ በህዝቡ ተመሳሳይ ግንዛቤ እንዲዳብር እያደረገ ይገኛል፡፡



*የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽ/ቤት አመራሮችና ሰራተኞች የሰንደቅ ዓላማን ቀን ሲያከብሩ*

በሰንደቅ ዓላማችን ፊት በቆምን ቁጥር የሀገሩ ምስል የማይከሰትበት ሰው የለም፡፡ ከአለም ታሪክ እንደምንረዳው ሀገራትና ዜጎች ከቅኝ ግዛት ተጽዕኖ ሲላቀቁ መጀመሪያ ከፍ

አድርገው የሚያሳዩት ሰንደቅ አላማቸውን ነው፡፡ ህዝቦችን አገራት በሰላም አደባባይም ሆነ በጦር ሜዳ ውሎ ለድል ሲበቁ ቅድሚያ የሚሰቅሉት ሰንደቅ አላማቸውን ነው፡፡ይህንን በማድረግ ፍቅርና ክብራቸውን እጅግ ከፍ ባለ መልኩ ለሰንደቅ አላማቸው ብሎም ለሀገራቸው ይገልጻሉ፡፡ እኛም ኢትዮጵያውያን ቀደምት አባቶቻችን ጣሊያንን ድል ሲነሱ ጀግኖች አትሌቶቻችን በኦሎሚፒክ፣ በቶክዮ በሌሎችም ሀገራት ሲያሸንፉ በሁሉም ድሎቻችን ሁሉ ሰንደቅ ዓላማችንን ከፍ ብላ እናያታለን የኢትዮጵያዊነት ጥልቅ ክብር፣ ጥልቅ ፍቅር የሚሰማን በሰንደቅ ዓላማችን ነው፡፡ ክብር ለሰንደቅ ዓላማችን ይሁን፡፡

## የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል አከባበር

‹‹ህብረ ብሔራዊ አንድነታችን ለዘላቂ ሰላማችን!›› በሚል መሪ ቃል የ17ኛው የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል ተከበሯል፡፡

ህብረ ብሔራዊ ፌደራላዊ ስርዓት የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራስ በራስ የማስተዳደር በቋንቋ የመናገር የማሳደግ፣ የመጻፍ፣ ባህልን የመግለጽ፣ የማዳበርና ማስፋፋት እንዲሁም ታሪክን የመንከባከብ ወ.ዘ.ተ. መብቶችን ለማረጋገጥና ለማክበር የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሚያዚያ 21 ቀን 1998 ዓ.ም ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል በህገ መንግስቱ በፀደቀበት ህዳር 29 ቀን እንዲከበር መወሰኑ ይታወቃል፡፡




የክብር እንግዶች አቀባበል

በሀገራች ለመጀመሪያ ጊዜ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን 1999 ዓ.ም በፌዴሬሽን ምክር ቤት አዘጋጅነት እንደ ሀገር አቀፍ በአዲስ አበባ ከተማ ተከብሯል፡፡ ይህንን ተከትሎ ክልሎችም በየተራ በየዓመቱ ሲያከብሩት የቆዩ ሲሆን አምና በድሬዳዋ አስተዳደር አስተናጋጅነት የ16ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል “ወንድማማችነት ለሕብረብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል በድሬዳዋ ከተማ ተከብሯል፡፡ በዘንድሮ ደግሞ የ17ኛው ‹‹ህብረ ብሔራዊ አንድነታችን ለዘላቂ ሰላማችን!›› በሚል መሪ ቃል ወቅታዊና ሀገራዊ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት ከሀገራዊ ምክክር ሂደቱ ጋር በማስተሳሰር የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀንን በሲዳማ ክልል አዘጋጅነት በሃዋሳ ከተማ ተከብሯል ፡፡




የአዲስ አበባ ከተማና ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤዎች የፓናል ውይይት የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ

እንደ አዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ሁነቶች የተከበረ ሲሆን ከከተማ እስከ ወረዳ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ያሳተፈ የፓናል ውይይት በማካሄድ፤በተማሪዎች የጥያቄና መልስ ውድድር እና በተለያዩ ሁነቶች ሲከበር ቆይቷል፡፡

ይህም ህዳር 24/2015 ዓ.ም ከተማ አቀፍ የማጠቃለያ ፓናል ውይይት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ አመራሮችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተገኙበት ተካሂዷል ።

በመድረኩም የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ቡዜና አልከድር እንዳሉት ህገ መንግስት የፀደቀበት ቀን በማክበር ብቻ ሳይሆን የህገ መንግስቱን መሠረታዊ ድንጋጌዎችና መርሆዎች ትርጉም ባለው ደረጃ መሬት ላይ አውርዶ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩ፤ የብልጽግና ጉዞ እየተከተለ ያለው የዲሞክራሲ አቅጣጫ በተለይ በትብብርና ውድድር ላይ የተመሠረተ ለብዝሃነትና ለህብረብሄራዊነት ልዩ ቦታ የሚሰጥ፣ ለህገ መንግስታችን የተመለከተውን እውነተኛ ህብረ ብሄራዊ ፌዴራሊዝም የመገንባት ዓላማ እንዲሁም በስርዓቱ ላይ ያለውን ህዝባዊ እምነት የሚፈታተኑ ችግሮችን በመቅረፍ እና ስርዓቱ ለዘላቂ ሰላም ግንባታ ያለውን ፋይዳ ለማረጋገጥ የሚያስችል መግባባትን ለመፍጠር ነው ሲሉ ተናግረዋል።




የ17 ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል ፓናል ውይይት መድረክ

በማስከተልም የዕለቱ የክብር እንግዳ የሆኑት የኢፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አቶ አገኘሁ ተሻገር በሀገራችን ለሩብ ምዕተ ዓመታት ህብረ ብሄራዊ የፌዴራል

ስርዓት ከተጀመረ አንስቶ ለብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በህገ መንግስቱ መነናጸፍ እንደመልካም አጋጣሚ የሚቆጠር ቢሆንም ከአተገባበሩ ጋር ተያይዞ ዴሞክራሲያዊነትና ፍትሀዊነት የተዛባ ትርክት በማስተላለፍ ይወቀሳል። ባለፋት አራት ዓመታት እነዚህን ችግሮች ለማረም እንቅስቃሴ እየተደረገ ሲሆን ብዝሀነትን ያከበረ አንድነት ለማረጋገጥ ብዙ መስራት እንደሚገባ ታውቆ በርካታ ተጨባጭ አዎንታዊ ውጤቶች ማስመዝገብ ጀምረናል ብለዋል።





የ17 ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል በመስቀል አደባባይ

ዕለቱን በማስመልከት በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የንግድና ኢንዱስቱሪና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ/ር አቶሜ አበበ አወያይነት ሰነድ ቀርቧል። በሰነዱ አሁን ያለውና ወደፊት የሚተካውን ትውልድ አንድነትና ትስስር ለማጎልበት፣ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ልምዳቸውን፣ ተሞክሯቸውን እና ባህላቸውን በመለዋወጥና ዴሞክራሲያዊ አንድነታቸውን በማጠናከር ለዘላቂ ሰላም ለልማትና ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት በአብሮነት እንዲሰለፉ ለማስቻል ትኩረት ያደረገ ሰነድ ቀርቦ ሰፊ ውይይት በማድረግ ተጠናቋል።






እንዲሁም ህዳር 25/2015 ዓ.ም የበዓሉ ማጠቃለያ በመስቀል አደባባይ በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት እና በክ/ከተማ ምክር ቤቶች አዘጋጅነት የተለያዩ የብሔር ብሔረሰቦች ባህል እና እሴቶች በሚወክሉ ህብረ ብሔራዊነት በሚያንጸባርቅ መልኩ በድምቀት ተከብሯል፡፡

በመድረኩ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ም/አፈ-ጉባኤ ፣የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ አመራሮች፣ የክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤዎችና የ11ዱም ክ/ከተማ ነዋሪዎች የተገኙ ሲሆን ህብረ ብሔራዊነት አንድነት፣በአስተሳሰብ ብዙ ሆኖ በአንድነት መኖር በሚያሳይ መልኩ የጋምቤላው፣ የሱማሌው፣የሀድያው የሌሎችም በአልባሳት፣ሀገራዊ ምግቦችና መጠጥ፣ አጨፋፈር የታጀበ ቀልብ በሚስብ የባህል ድባብ የታየበት ነበር፡፡



የ17 ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል የምግብ አውደ ርዕይ

በበዓሉ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ምክትል አፈጉባኤ የተከበሩ ወሪ/ት ፋይዛ መሐመድ እንዳሉት ሀገራችን ኢትዮጵያ በአለም የምትታወቀው በምድረ ቀደምትነቷ የሰው ዘር መገኛ እንደመሆኗ ያለንን ባህል ሀይማኖት እሴት ለማስቀጠል ብሎም በልዮነት አንድነት፣ በአንድነት ሃገራዊ ህብረ ብሄራዊ አንድነትን ለማጠናከር ይህ በዓል ትልቅ ሚና አለው ሲሉ ተናግረዋል። በመቀጠልም የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ተወካይ እና የአዲስ አበባ ከተማ መሬት ማኔጅመት ቢሮ ሀላፊ ዶ/ር ቀናዓ ያደታ አንድነታችንን የሚፈታተኑ የብሔር ስም ፅንፈኞች ፣የሀይማኖት ፅንፈኞች፣ የማንነት ፅንፈኞች ፣ሙሰኝነትና ድህነት የኢትዮጵያ ጥንካሬ ጠንቅ ስለሆኑ ትኩረት ሰጥተን ልንታገል ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡



በመስቀል አደባባይ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን አከባበር የመክፈቻ ንግግር

ህዳር 29/2015 ዓ.ም ደግሞ በአገር አቀፍ ሀዋሳ ከተማ የተከበረ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የትግራይን ወግ እና ባህል የሚያስተዋውቁ የባህል ልዑካን ቡድን በመምራት የባዓሉ ታዳሚ ሆኗል፡፡በእለቱም የክብር እንግዳ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ

**አህመድ ፤ቀዳማዊ እመቤት ዝናሽ ታያቸው እና ሌሎች ሚኒስትሮች ፤የክልል ፕሬዝዳትና ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት የሁሉንም ብሄር ብሄረሰቦችን ባህል በሚያሳይ መልኩ በድምቀት ተከብሯል፡፡**



የ17 ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል በሀዋሳ



*የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በሐዋሳ ከተማ ሲከበር*

## አረንጓዴ አሻራ ልማት  ለሀገር እና አካባቢ ልማት

የአንድ ሀገር አረንጓዴ ልማት ለጤናማ አካባቢና የአየር ንብረት ጉልህ ሚና አለው በአረንጓዴ ልማት እጦት አለማችን በበርካታ የተፈጥሮ አደጋዎች ስትጠቃ አስተውለናል፡፡ ከትንሹ ወቅቱን ካልጠበቀ ዝናብ እስከ ዝናብ እጥረት ምክንያት በሀገራችን እንኳ በርካታ የሰው ልጅን ህይወት የቀጠፉ የረሀብና ድርቅ አደጋዎችን አስተናግዳለች፡፡ ታድያ ለዚህ ችግር በዋነኝነት በምክንያት የሚጠቀሰው የደኖች መመናመንና የአካባቢ መራቆት ሲሆን የሰውልጅ ሚዛኑን በጠበቀ የአየር ንብረት መኖር ተጠቃሚው እራሱ ሆኖ ሳላ የሰው ልጅ እራሱ ለደኖች መመናመንና ለአካባቢ መራቆት ግንባር ቀደም ሆኖ ስሙ ሲጠቀስ ይስተዋላል፡፡



ያልተገባ የደን ጭፍጨፋ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ቀደም ሲል ለምለሚቷ ኢትዮጵያ የሚል ስያሜ ያሰጣት በውስጧ ያሏት የተፈጥሮ ዕፅዋትና የደን ሽፋን ቢሆንም ከጊዜ ጊዜ እየጨመረ የመጣው የአካባቢ መራቆትና የደን ሽፋን መመናመን ምክንያ ሀገራችን ኢትዮጵያ ባጋጠሟት የዝናብ እጥረትና ድርቅ ምክንያት በርካታ ችግሮችን አሳልፋለች፡፡ ይሁን እንጂ መንግስታት በተለያየ ወቅት ችግሩን እልባት ለመስጠት ይበጃል ያሏቸውን መፍትሄዎች ለመውሰድ ሞክረዋል፡፡



የደን ጭፍጨፋና አካባቢያዊ ተፅዕኖ

የተፈጥሮ ዕፅዋት የብዝሀ ህይወት ጥበቃ ተቋማት ከማቋቋም እስከ ደኖችን ጥብቅ ደን እስከ ከማድረግ መፍትሄ ያሏቸውን አማራጮች ተጠቅመዋል፡፡



ምክር ቤቱ በኢፌድሪ አየር ኃይል ጠቅላይ መመሪያ ግቢ ውስጥ አረንጓዴ የልማት አሻራ ሲያሳርፉ

ከለውጥ ወዲህ የሀገራችንን የደን ሽፋን በማሳደግ ረገድ ልዩ ትኩረት በመስጠት የተቆራረጠና ወጥ ያልሆነውን የዛፍ ችግኝ ተከላ ፕሮግራም ስርዓት በማስያዝ እና ሀገራዊ ትኩረት በመስጠት ዘላቂ የአረንጓዴ ልማት ኢኮኖሚ ለመፍጠር ተሞክሯል፡፡ በዚህ ዓመት ብቻ ነገን ዛሬ እንትከል በሚል መርህ በአንድ ጀምበር 500 ሚሊየን ችግኝ እንትከል በሚለው ሀገር አቀፍ መርሃግብር ምክር ቤቱ

ዋነኛ ተዋናይ በመሆን ከከተማ እስከ ወረዳ ባሉ የምክር ቤት መዋቅር አረንጓዴ የልማት አሻራውን በማሳረፍ የበኩሉን ሚና ተወጥቷል፡፡



*የምክር ቤት አባላት በለሚኩራ አሲቲ ፓርክ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ሲያከናውኑ*

ምክር ቤቱ በዚህ አረንጓዴ  አሻራ ልማት ማሳረፍ ተግባር ውስጥ በኢፌዲሪ አየር ኃይል መምሪያ ቅጥር ግቢ ውስጥ አረንጓዴ የልማት አሻራ ከማሳረፍ ባሻገር የተተከሉ ችግኞችን በመንከባከብ የፅድቀት መጠናቸውን በመጨመር ለአካባቢ የአየር ንብረት መጠበቅ ያገባኛል የሚል መሆኑን አሳይቷል፡፡



*የምክር ቤት አባላት ከሀይማኖት አባቶች ጋር የካ ሚሊኒየም ፓርክ አረንጓዴ አሻራ ሲያከናውኑ*

ምክር ቤቱ የእህት ከተሞች ትስስርን ከመፍጠር አኳያ በምክር ቤቱ አፈ ጉባዔ እየተመራ በኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አባላትን በማስተባበር የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር ያካሄደ ሲሆን መርሀ ግብሩን የመሩት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ቡዜና አልከድር መርሃ ግብሩን ባስጀመሩበት ወቅት እንዳሉት አዲስ አበባ የሁላችን ከተማ እንደመሆኗ መጠን አሻራዋን በሁሉም ከተሞች ታኖራለች፤ ይህ ደግሞ የህዝቦችን በጋራ አብሮ የመኖርና የማደግ ትስስርን የሚያጠናክር መሆኑን ገልፀዋል፡፡



የምክር ቤት አባላትና አመራሮች በአዳማ ከተማ አረንጓዴ የልማት አሻራ ሲያሳርፉ

በሌላ በኩል በአንድ ጀምበር 500 ሚሊየን ችግኝ እንትከል በሚለው ሀገር አቀፍ መርሀ ግብር የምክር ቤት ጽ/ቤት አመራና ሰራተኞች የተሳተፉ ሲሆን በዚሁ እለት በአዲስ አበባ ከሀያት ጣፎ አደባባይ አሻራቸወን አኑረዋል፡፡



የምክር ቤት ጽ/ቤት አመራርና ሰራተኞች አረንጓዴ የልማት አሻራቸውን ሲያሳርፉ

በጥቅሉ በዛም ሆነ በዚህ እነዚህ የአረንጓዴ የልማት አሻራዎች ለሀገር ትልቅ ፋይዳ የሚኖራቸው የተተከሉ ችግኞች ፀድቀው የአካባቢንና የሀገርን ተፈጥሯዊ ስነ ምህዳር ሚዛን መጠበቅ ሲችሉና የተስተካከ የአየር ንብረት መፍጠር ሲቻል በመሆኑ ምክር ቤቱ የተተከሉ ችግኞችን በመንከባከብ የታለመለትን አላማ ማሳካት እንዲችሉና እንደስሟ ለምለም የሆነች ሀገር በመስራት በኩልና እንደ ስሟ ውብና አበባ የሆነች ከተማን በመፍጠር ረገድ  በዘላቂ የአረንጓዴ ልማት ስራዎች ላይ በትኩረት ይሰራል፡፡

## የክፍለ ከተማ እና ወረዳ ምክር ቤቶች እንቅስቃሴ

አሁን በስራ ላይ ያሉት የክፍለ ከተማ ም/ቤት አመራርና አባላት የአግልግሎት ዘመናቸው ረዘም ያለና ከ10 ዓመታት በላይ ያገለገሉ ሲሆኑ በተግባር አፈፃፀማቸውም የመራጩን ህዝብ ፍላጎትና ጥያቄዎች በትክክል የሚያውቁና የትኛው ጥያቄ በማንና የት መፈታት እንደሚችል

ሁሉ ተረድተው እንዲፈቱ በማድረግም ከጊዜ ወደ ጊዜ አዳጊ ለውጦችን እያስመዘገቡ የመጡ ናቸው፡፡





*በክፍለ ከተማ ምክር ቤቶች በመደበኛ ጉባኤ ላይ*

በ2015 በጀት ዓመት የም/ቤት አመራሩ በክ/ከተማና በወረዳ ደረጃ ያሉ ም/ቤቶችን በመምራትና በማስተባበር የ2014 ዓ.ም አፈፃፀምን በመገምገምና የመልሶ ማደራጀት ስራዎችን በየአደረጃጀቶቹ አመራሮችን ማጠናከር የቻሉ ሲሆን ሁሉም የም/ቤት አባላት በትስስር አደረጃጀቶቻቸው አማካኝነት ሂሲ ግለሂስ አድርገው በግምገማ እንዲያልፉ በማድረግ ለቀጣይ 2015 ዓ.ም ተልዕኮ በክ/ከተማም በወረዳም የተሟላ ዝግጅት እንዲኖራቸው አድርገዋል፡፡

በተመሳሳይ የ2015 ዓ.ም የከተማውን መሪ እቅድ መነሻ በማድረግ በሁሉም ም/ቤቶች ያሉ አደረጃጀቶች የየራሳቸውን እቅድ በማዘጋጀት በየደረጃው ግልፅ ኦረንቴሽን በመስጠት ወደ ስራ ገብተዋል፡፡





*በክፍለ ከተማ ምክር ቤቶች በመደበኛ ጉባኤ ላይ*

በተግባር አፈፃፀምም የም/ቤት አመራሩ ዓመታዊ እቅዳቸውን መሰረት በማድረግ የም/ቤት መደበኛ ጉባኤዎችን በተቀመጠላቸው ጊዜ ወቅቱን ጠብቀው በማካሄድ ከም/ቤት ጉባኤ የሚጠበቁ ውሳኔዎችን ማስተላለፍ የቻሉ ሲሆን የአስፈፃሚውን ሪፖርትና በዘርፍ ኮሚቴ የታዩ ክፍተቶችንም እንዲስተካከሉ አቅጣጫ በማስቀመጥና በክትትል ላይ የተመሰረተ እርምጃ መውሰዱንም በማመላከት ለመራጩ ህዝብም መረጃዎች ማድረስ ችለዋል፡፡

ፎቶ

እንደ ከተማ በተዘጋጁ ሁነቶችና በዓላት የወረዳና የከተማ ም/ቤቶችና ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማስተባበር ውጤታማ ስራዎችን ማከናወን የቻሉ ሲሆን የዘርፍ ኮሚቴዎችና የትስስር አደረጃጀቶችም በእቅዳቸው መሰረት በደረጃቸው ያሉ የአስፈፃሚ አካላትን ቁጥጥር ክትትልና ድጋፍ ስራዎቻቸውን እንዲሁም የትስስር አደረጃጀት አመራሮች የም/ቤት አባላት በየተደራጁበት የምርጫ ክልል አደረጃጀት መሰረት ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ማዕድ በማጋራት፣ የአቅመደካሞችን ቤት ጥገናና እድሳት፣ ልዩ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ህፃናቶችን በመደገፍ፣ ከተማ አቀፍና ካባቢያዊ የህዝብ ንቅናቄ ስራዎች የልማት፣ የሰላምና ፀጥታ፣ የታላቁ ህዳሴ ግድብ የሀብት አሰባሰብ፣ የከተማ ግብርና ስራዎች፣ የአረንጓዴ አሻራ የአካባቢ ጥበቃና ከተማ ውበት ስራዎች ላይ የክ/ከተማ ም/ቤቶችንና የወረዳ ም/ቤት አመራሮችን በማስተባበር የም/ቤቶችን ቅቡልነትና ህዝባዊ ኃላፊነት በግልፅ ማሳየት ችለዋል፡፡



*የክፍለ ከተማ ምክር ቤቶች በጉብኝት ላይ*

የም/ቤት አመራሩ ከላይ የተገለፁትን ውጤቶች በየጊዜው በአስተባባሪ ኮሚቴ ስራዎችን በመገምገምና መደበኛ የግንኙነት ጊዜዎችን ከተዋረድ አደረጃጀቶች ወደ ላይ ከከተማ ም/ቤትና

ወደታች ከወረዳ ም/ቤት እና በተጓዳኝ ካሉ የዘርፍና የትስስር አደረጃጀቶች ጋር ስራን በቅርብ በመገምገም ከላይ አቅጣጫዎችን በመቀበልና ወደጎንና ወደታች አቅጣጫዎችን በመስጠት የተሻለ አፈፃፀም የተመዘገበበት ነው፡፡

የም/ቤት አባላቱም ከላይ በተጠቀሱት አደረጃጀቶችና ስራዎች ተሳታፊና ባለቤት በመሆን አርዕያነት ያለው የህዝብ ተመራጭነት ውክልና ኃላፊነታቸውን በመወጣት በመራጩ ህዝብን አመኔታን በም/ቤቶችም ተቀባይነትን ማሳየት ያቻሉ ለ2016 ዓ.ም ስራም እንደ መነሻ የሚወሰዱ ውጤቶች ያሳዩ ናቸው፡፡



*በክፍለ ከተማ ምክር ቤቶች በመደበኛ ጉባኤ ላይ*

አበረታች አፈፃፀሞች የሚጠናከሩ ሆኖ ለቀጣይ ስራ የሚጠይቁ የም/ቤት አመራርና አባላቱ ለረጅም ጊዜ መቆየታቸው በተለያየ ምክንያት ቁጥራቸው በመቀነሱ እስከ ምልዓተ ጉባኤ መሟላት ላይ ጭምር ስጋት እስከ መሆን መድረስና በአንዳንድ ም/ቤቶች የመሰላቸት ዝንባሌዎችም የተስተዋሉ መሆናቸው፣ በተለያዩ የዘርፍ ኮሚቴዎችና የም/ቤት አደረጃጀቶች ለመስራት አለመፈለግና ያለመገኘት፣ ሁሉም የም/ቤት አባላት በሁሉም የስራ ተሳትፎዎች የም/ቤት ጉባኤን ጨምሮ ያለመሳተፍና ያለመገኘት፣በአንዳንድ አደረጃጀቶች በተቀመጠው የግንኙነት ጊዜ ወቅቱን ጠብቆ ያለመገናኘት ማቆራረጥ የሚሉት ለቀጣይ ዓመት ትኩረት ተሰጥቶ መስተካከል ያለባቸው ናቸው፡፡

ፎቶ

| ተ.ቁ | በ2015በጀት ዓመት የተካሄዱ ጉባኤዎችና አጀንዳዎቻቸው | |
|---|---|---|
| | **የታካሄዱበት ወቀቶች** | **የፀደቁ አጀንዳዎች** |
| 1 | **በ2ኛ ዓመት የስራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ጉባኤው ጥቅምት 04/2015ዓ.ም** | ➢ የምክር ቤቱ 1ኛ ዓመት የስራ ዘመን 3ኛ መደበኛ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ ላይ ተወያይቶ አፅድቋል፤<br>➢ .የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ተወያይቶ አፅድቋል፡፡<br>➢ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ለከተማ አስተዳደሩ ስድስት የቢሮ ኃላፊዎችና 49 ዳኞች ለአዲስ አበባ ከተማ ፈርድ ቤትና በተዋረድ ላሉ የፍርድ ቤት ዳኞች ከክብርት ከንቲባዋ የይፅደቅልኝ ጥያቄ አቅርበው ምክር ቤቱ የእጩ ተሸሚዎችን የስራ ልምድና ክህሎት መርምሮ ሽመቱን አፅድቋል፡፡<br>➢ ምክር ቤቱ የአንድ የምክር ቤት አባል ያለመከሰስ መብት አንስቷል፡፡ |
| 2 | **በ2ኛ ዓመት የስራ ዘመን 3ኛ መደበኛ ጉባኤው መጋቢት 5/2015 ዓ.ም** | ➢ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚ አካላት ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 74/2014 እንደገና ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ አዋጅ ተወያይቶ አፅድቋል፡፡<br>➢ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የክፍለ ከተማና ወረዳ የምክር ቤት የመርጫ ክልል እና የሚመረጡ አባላትን ቁጥር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ተወያይቶ አፅድቋል፡፡<br>➢ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽ/ቤት ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ ተወያይቶ አፅድቋል፡፡<br>➢ በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ የቀረበለትን የተለያዩ አስፈፃሚ አካላትና ልዩ ልዩ ሹመቶችን አፀድቋል፡፡<br>➢ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር ቢሮ የሰራተኞች አስተዳደር ደንብ አፀድቋል፡፡<br>➢ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፀረ ሙስና ኮሚሽን መተዳደሪያ ልዩ ልዩ ደንቦች ፀድቋል፡፡ |
| 3 | 2ኛ ዓመት የስራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባኤውን **ሀምሌ** 2/2015 ዓ/ም | ➢ የከተማ አስተዳደሩን የ2015 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት፣<br>➢ የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ኦዲተር የ2015 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት፣<br>➢ የከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶችን የ2015 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እና<br>➢ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2016 ረቂቅ የበጀት አዋጅ ላይ ተወያይቶ በማፅደቅ ጉባኤውን አጠናቋል፡፡ |

| ተ.ቁ | አዋጅ ቁጥር | የአዋጁ መጠሪያ |
|---|---|---|
| 1 | 1/2000 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 2/1995 እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ |
| 2 | 3/2000 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2001 ዓ.ም የበጀት አዋጅ |
| 3 | 4/2000 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 4 | 5/2000 | የከተማው አስተዳደር አካላት አስተዳደሩን ቤቶች ማስተላለፍ ሀላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 19/1997 እንደገና ማሻሻያ አዋጅ |
| 5 | 6/2000 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ |
| 6 | 7/2001 | የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ሀላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 19/1997 እንደገና ማሻሻያ አዋጅ |
| 7 | 8/2001 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ አስተዳደርና አመራር ማሻሻያ አዋጅ |
| 8 | 10/2001 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናትን ለመተግበር የወጣ አዋጅ |
| 9 | 11/2001 | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 10 | 12/2001 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 11 | 13/2001 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2001ዓ.ም ተጨማሪ በጀት አዋጅ |
| 12 | 14/2001 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2002ዓ.ም በጀት አዋጅ |
| 13 | 15/2001 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ |
| 14 | 16/2002 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ |
| 15 | 17/2002 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ |
| 16 | 18/2002 | የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 17 | 19/2002 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጨማሪ የበጀት አዋጅ |
| 18 | 20/2002 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲን ለማቋቋማ የወጣ አዋጅ |
| 19 | 21/2002 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አካላትን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/2001 ለማሻሻል የወጣ አዋጅ |
| 20 | 22/2002 | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 21 | 23/2002 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበጀት አዋጅ |
| 22 | 24/2003 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 22/2002 ማሻሻያ አዋጅ |
| 23 | 25/2003 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/2001ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ |
| 24 | 26/2003 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2004 በጀት ዓመት የበጀት አዋጅ |
| 25 | 27/2003 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አካላትን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ 15/2001ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ |

| | | |
|---|---|---|
| | | አዋጅ |
| 28 | 28/2004 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አካላትን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ 15/2001ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ |
| 29 | 29/2004 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 30 | 30/2004 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ መድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 31 | 31/2004 | የየካቲት 12 ሆስፓታል ሜዲክል ኮሌጅ ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 32 | 32/2004 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጨማሪ የበጀት አዋጅ |
| 33 | 33/2004 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበጀት አዋጅ |
| 34 | 34/2004 | የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ፅህፈት ቤት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ |
| 35 | 35/2004 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ |
| 36 | 36/2004 | ከሀላፊነት የሚነሱ የአዲስ አበባ ከተማ መሪዎች፣ ከፍተኛ ሀላፊዎች፣ በቋሚነት የሚሰሩ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅ |
| 37 | 37/2005 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ |
| 38 | 38/2005 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጨማሪ የበጀት አዋጅ |
| 39 | 39/2005 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበጀት አዋጅ |
| 40 | 40/2006 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2006 ዓ.ም ተጨማሪ የበጀት አዋጅ |
| 41 | 41/2006 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበጀት አዋጅ |
| 42 | 42/2006 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 20/2002ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ |
| 43 | 43/2007 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገሌግልት አካላትን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፩ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ |
| 44 | 44/2007 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበጀት አዋጅ |
| 45 | 45/2007 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ |
| 46 | 46/2008 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግልት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፩ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ |
| 47 | 47/2008 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2009 የበጀት አዋጅ |
| 48 | 48/2009 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላን ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር (48/፪ሺ9 |
| 49 | 49/2009 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮና የማሰልጠኛ ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 50 | 50/2009 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበጀት አዋጅ ቁጥር 50/2009 |
| 51 | 51/2009 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር16 ፪ሺህ፪ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 51/2009 |
| 52 | 52/2009 | የአዲስ አበባ መዋቅራዊ ፕላን |

| | | |
|---|---|---|
| 53 | 53/2009 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሠረተ ልማት ቅንጅትና የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ |
| 54 | 54/2009 | የአዲስ አበባ ማዕከላትና ኮሪደሮች ልማት ኮርፖሬሽንማቋቋሚያ |
| 55 | 55/2009 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 20/2ሺህ2 (እንደተሻሻለ) እንደገና ለማሻሻል የወጣ |
| 56 | 56/2010 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ |
| 57 | 57/2010 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሳይንስናቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 58 | 58/2010 | የአዱስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገሌግልት አካላትን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺህ፱ እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ |
| 59 | 59/2010 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል አከባበር ምክር ቤትና የበዓል ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 60 | 60/2010 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበጀት አዋጅ |
| 61 | 61/2010 | ከኃላፊነት የሚነሱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ ሌሎች ኃላፊዎች፣ በቋሚነት የሚሠሩ እና ሌሎች የምክር ቤት አባላትና ዳኞች የሚያገባቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለመተካት የወጣ አዋጅ |
| 62 | 62/2010 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተፋሰስ እና አረንጓዴ አካባቢዎች ኤጀንሲማቋቋሚያ አዋጅ |
| 63 | 63/2010 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/፪ሺህ፱ (እንደተሻሻለ) እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ |
| 64 | 64/2011 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 65 | 65/2011 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትወርክ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 66 | 66/2011 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበጀት አዋጅ |
| 67 | 67/2012 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ ማሻሻያ አዋጅ |
| 68 | 68/2012 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 69 | 69/ 2012 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እንደገና ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 29/2004 ማሻሻያ አዋጅ |
| 70 | 70/ 2012 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 64/2011 እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ |
| 71 | 71 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2013 በጀት አዋጅ |

| | | |
|---|---|---|
| 72 | | |
| 73 | 73/2013 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2014 በጀት አዋጅ |
| 74 | | |
| 75 | 75/2014 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 76 | 76/2014 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2015 በጀት |
| 77 | 77/2014 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ |
| 78 | 78/2014 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዢና ንብረት አስተዳደር ማሻሻያ አዋጅ |

# ፎቶ ማህደር






































3ኛው
የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት
2ኛ ዓመት የስራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ጉባኤ
ጥቅምት 4/2015 ዓ.ም




















Radisson BLU
HOTEL, ADDIS ABABA




























‹‹የአራዳ ክ/ከተማ
ምክር ቤት 2ኛ ዙር 10ኛ
ዓመት የሥራ ዘመን 2ኛ
መደበኛ ጉባኤ››
2015 ዓ.ም
Your City Retreat!




“የአራዳ ክፍለ ከተማ





**ዋና አዘጋጅ**

**አዲስአለም እንቻለው**

## አዘጋጆች

ሙሉብርሃን ገ/መድህን

ነፃነት ብርሀኑ

ውዴ ታደሰ

**ካሜራ ባለሞያ**

ሀ/ማርያም መንግስቱ

ሮማን ገዛህኝ

**ህትመት ክትትል**

ትህትና አበበ